# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*

ሚያዝያ 13/2003

## የወያኔ መሰረተ ቢስ ክስ አድማጭ አያገኝም

በውሸት የተካነው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በወጣት ማህበር ደረጃ አደራጅቻለሁ የሚላቸውን ወጣቶች እየሰበሰበ በአባይ ላይ ትልቁን ግድብ እንዳንሠራ ኢሕአፓ ከግብፅ ጋር አብሮና ተመሳጥሮ ሻጥር እየፈፀመ ነው ብሎ ያሰራጨው ክስ አድማጭም ሆነ ተቀባይ የሚያገኝ አልሆነም። ኢሕአፓ ከዚህ ቀደም በጣና በለስ ግድብ ሊሠራ ሲል የተቋራጩን ጣሊያን ኩባንያ ሠራተኞች ጠልፎ ሥራውን አደናቅፏል ብሎ ክሱን ሊያጣፍጥና አሳማኝ ለማስመሰል እየሞከረ ያለው ፀረ ሕዝብ አገዛዝ ተልዕኮውና ጥረቱ የሚሳካለት አይሆንምም ተብሏል።

ኢሕአፓ የወያኔ የግድብ ግንባታ ጫጫታ አንድም ሕዝብን ከወሳኙ ፍልሚያ አደናግሮ ለማራቅና በተጨማሪም ደግሞ ሕዝብን ለመዝረፍ ነው በሚል ተቃውሞውን በግልፅ አስቀምጧል። ኢሕአፓ በደርግ ዘመን በጣና በለስ ይደረግ የነበረውን እንቅስቃሴ የተቃወመው ለምንስ ግድብ ተሰራ በሚል ሳይሆን ከአንጉል ሰፈራና ለወታደራዊ ግልጋሎት ሊሰሩ ከተጀመሩ መንገዶች ጋር በተያያዘ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ግብፅ የማን ወዳጅ ነው ከተባለም ታሪክ የሚሰጠው መልስ የወያኔና የገንጣዮች የሚል እንጂ የኢሕአፓ የሚል አይደለም። ከዚህ ባሻገር ደግሞ ማን ነው ሀገሩን የከዳ? ማነው የሀገሩን መሬት ለባዕድ አሳልፎ የሰጠ? ማነው ፀረ-ኢትዮጵያ? ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ ወያኔና መለስ ዜናዊ የሚል መሆኑን ሁሉም ዜጋ ያውቃል። አባይን በትልቁ ለመገደብ ወያኔ ብቃቱም የሕዝብ አመኔታም እንደሌለው ደግሞ ባለጉዳዩ ሕዝብ ሁሉ የሚያውቀው ሐቅ ነው። ይህ ሁሉ ያውም ግድቡ ሲሰራ ስለሚፈናቀለው ሕዝብ ምንም ሳናነሳ ነው።

የመለስ አገዛዝ ያደናገረ መስሎት ወጣቶችን በተከታታይ እየሰበሰበ በኢሕአፓ ላይ የሚያዘንበው ክስ ወጣቶችን የሚያደናግር እንደማይሆን ከወዲሁ የሚታወቅ ነው። ተመሳሳይ ቅስቀሳና ክስ በሠራዊቱም ውስጥ መጀመሩ ታውቋል። የዚህ አረመኔ አገዛዝ የገደል ማሚቴዎችም በሀገር ቤትና በውጭ ሀገር ኢሕአፓን ለማጥላላትና ከሕዝብ ለመነጠል እያደረጉ ያለውን ጥረት ዜጎች ሁሉ እያታዘቡት ያለ ነው። ወያኔም ፍኖተ ዴሞክራሲ ራዲዮን ማፈኑ ምን ያህል የኢሕአፓን ድምፅና ቅስቀሳ እንደሚፈራ ገላጭ ነው። የኢሕአፓ የወጣት ሊግ ማለትም ወክንድ እያደረገ ያለው ገንቢ እንቅስቃሴ ለወያኔ መርዶ መሆኑም በዚሁ ይታያል። የሀሰት ክስ ሀገር ሁሉ የሚያውቀውን ሐቅ ከቶም ሊደብቅ አይችልም--ፀረ ኢትዮጵያው አረመኔ ከሀዲ፣ ባንዳና ማፈሪያ ኃይል ወያኔ ራሱ ነው።

አምፁ! ድል የሕዝብ ነው!!


EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com